የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 7 እና 8

ነ. ከሚከተሉት ውስጥ ማርያም እንተ እፍረት ካደረገቸው ነገር የምንማረው የቱን ነው?
ሀ) በዕንባዋ የጌታችንን እግር ማጠቧ ንስሐን ያስተምረናል
ለ) በራስ ጸጉሯ የጌታችንን እግር ማበሷ ትሕትናን ያስተምረናል
ሐ) የጌታችንን እግር መሳሟ ፍቅርን ያስተምረናል
መ) ዋጋው ውድ የሆነ ሽቱ የጌታችንን እግር መቀባቷ አክብሮን ያስተምረናል
ሠ) ሁሉም መልስ ናቸው

2. ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅፍርናሆም ያደረገው ተአምር የቱን ነው?
ሀ) የጎጢአተኛዋን በደል ይቅር ማለት
ለ) የመበለቷን ልጅ ከሞት ማስነሳት
ሐ) የመቶ አለቃውን አገልጋይ መፈወስ
መ) መጥምቁ ዮሐንስን ደቀመዛሙርቱን ልኮ ከእስር ማስፈታት

3. ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በናይን ያደረገው ተአምር የቱን ነው?
ሀ) የጎጢአተኛዋን በደል ይቅር ማለት
ለ) የመበለቷን ልጅ ከሞት ማስነሳት
ሐ) የመቶ አለቃውን አገልጋይ መፈወስ
መ) መጥምቁ ዮሐንስን ደቀመዛሙርቱን ልኮ ከእስር ማስፈታት

4. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 7 የመስፍኑ ሎሌ በታመመ ጊዜ መስፍኑ ምን አደረገ?
ሀ)እራሱ መጥቶ ያድንለት ዘንድ ለመነው
ለ)የአይሁድ ሽማግሌዎችን ወደ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ላከ
ሐ)ሎሌውን ተሸክሞ ወደ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ይዞ መጣ
መ)ሀ እና ሐ

5. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 7 ጌታችን የመበለቲቱን ልጅ በምን ሁኔታ ላይ እያለ አዳነው?
ሀ)ታሞ በአልጋ ላይ ሳለ
ለ)ሞቶ በእናቱ እቅፍ ሳለ
ሐ)ሞቶ ሬሳውን ተሸክመው ሲሄዱ
መ)ሁሉም

6. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 7 ላይ ጌታችንን በማዕድ የተቀመጠው በማን ቤት ነው?
ሀ)በስምዖን
ለ)በባለሽቱዋ ማርያም
ሐ)በመስፍኑ ሎሌ
መ)ልጇን ባዳነላት መበለት ቤት

7. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ላይ ጌታችን ተዘዋውሮ ሲያስተምር አብረውት ከነበሩት ውስጥ የማይጠቀሱት እነማን ናቸው?
ሀ)ነ2ቱ ሐዋርያት
ለ)መግደላዊት ማርያም ሶስና ዮሐና
ሐ)መጥመቁ ዮሐንስ
መ)ሁሉም

8. ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ሌጌዎን የተባሉትን አጋንንት ያወጣቸው በየት ነው?
ሀ)ጌርጌሴኖን ለ)ናይን ሐ)ናዝሬት መ)ሁሉም

9. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 7 እና 8 በአጠቃላይ ስንት ሰው ከሞት አስነሳ?
ሀ) አንድ ለ)ሁለት ሐ)ሦስት መ)አራት

ነ0.የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ልብስ በመዳሰስ የዳነችው ሴት ስንት ዓመት ደም ይፈሳት ነበር?
ሀ)9 ለ)ነ0 ሐ)ነነ መ)ነ2

ነነ. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ላይ ሐዋርያት የነበሩበት መርከብ በአውሎ ንፋስ ሲናወጽ ጌታ በየት ነበረ?
ሀ) በተራራ ሲጸልይ ቆይቶ
ለ) ሕዝቡን አሰናብቶ እየተመለሰ
ሐ) ተኝቶ
መ) ሀ እና ለ

ነ2."በእሾህ መካከል የወደቀው ዘር " ምሳሌነቱ ለምንድን ነው?
ሀ) ሰምቶ ለጊዜው ደስ ብሎት የሚቀበል፤ መከራና ስደት ሲሆን ፈጥኖ የሚከድ
ለ) ቃሉን ሰምቶ ያላስተዋለ፣ ዲያብሎስ መጥቶ በልቡናው የተዘራውን የሚያጠፋበት
ሐ) ሰምቶ፣ አስተውሎ የሚሰራ
መ) ቃሉን ሰምቶ የዚህ አለም ሃሳብ እና የሃብት ማታለል አንቆት ያለ ፍሬ የሚቀር

ነ3.ዘር እና ዘሪ ተብለው የተመሰሉት ምንድን እና ማን ናቸው?
ሀ) ቁርባን እና ሐዋርያት
ለ) ወንጌል እና ጌታችን
ሐ) ዕጣን እና መላእክት
መ) ብሉይ ኪዳን እና ሐዋርያት

14.በጭንጫ ላይ የወደቀው ዘር ትርጉም ምንድን ነው?
ሀ) በመጀመርያ ቃሉን በደስታ የሚቀበለው ነገር ግን በቃሉ ምክንያት መካራ ሲመጣ መቋቋም ሚያቅተው
ለ) ከፉ ዲያቢሎስ የተማረውን ቃል ሳያድግ የሚወስድበት
ሐ) ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል
መ) መልስ አልተሰጠም

15.በመንገድ ዳር የተዘራው ዘር ምሳሌ ላይ ወፎች ተብለው የተጠቀሱት ምንድን ናቸው?
ሀ) ቅዱሳን መላእክት
ለ) ከፉ(አጋንንት)
ሐ)ርግቦች
መ)ሁሉም

16.ዘሪ ዘሩን ከዘራባቸው ቦታዎች ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) መንገድ ላይ
ለ)ጭንጫ ላይ
ሐ)ወፎች ጎጆ ውስጥ
መ)እሾህ መካከል

17.ከሴቶች ከሚወለዱ ወገን የሚበልጠው የለም የተባለለት ማን ነው?
ሀ) ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ
ለ) መጥምቁ ዮሐንስ
ሐ) ጴጥሮስ
መ) ኤልያስ

18.አስቀድሞ የመጥምቁ ዮሐንስ፣ ኋላም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙር የነበረው የቱ ነው?
ሀ) ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ
ለ) እንድርያስ
ሐ) ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ
መ) ለ እና ሐ

19.በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 7 "በእስራኤልስ እንኳ እንዲህ ያለ እምነት አላገኘሁም" የተባለለት ማን ነው?
ሀ) ጴጥሮስ
ለ) ሎሌው የታመመበት መስፍን
ሐ) ዮሐንስ
መ) ይሁዳ

20. ጌታችን በገሊላ አውራጃዎች እየዞረ ሲያስተምር ይከተሉት ከነበሩት ሴቶች ውስጥ የማትካተተው የትኛዋ ናት?
ሀ) መግደላዊት ማርያም ለ) ዮሐና ሐ) ሶስና መ) ማርታ ሠ) ሀ እና መ